# ይድረስ ለወያኔ/ኢሕአዴግ የጦርና የደኅንነት መዋቅር አባላት

ኀሊና ይሄይስ - አዲስ አበባ

የሁሉም ዘመን ሰው መሆን ይቻላልን? እንዴታ! በደንብ ይቻላል፡፡

አቶ ጌታቸው አሰፋና የወያኔ ደኅንነት መዋቅር አባላት እንዲሁም ሌሎች መለዮ ለባሾችና የመከላከያ ሠራዊቱ አባላት ለጋራ ኅልውናና ለእውነት ስትሉ እባካችሁን ይህችን ከቀድሞ የሥራ ባልደረባችሁ የተላከች መልእክቴን በሚገባ አድምጡኝ፡፡ ‹ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ› ነውና ከራሴው ከቀድሞ የሁለት መንግሥታት የፀጥታና የሀገር ደኅንነት አባል አንደበት የምነግራችሁን በጥሞና ተከታተሉኝ - ከታሪክ፣ ከትውልድና ከእግዚአብሔር(ከአላህ) ፍርድ ለመዳን ከፈለጋችሁ ለምለው እያንዳንዱ ነገር ጆሮ ስጡ፤ ለጊዜው ከደኅንነት ሥጋት አንጻር ስሜን ብለውጥም ታሪኬ እውነት ነው፡፡ ዕድሜ ለአነፍናፊው የሀገራችን የስለላ መረብ ለቁም ነገር ቀርቶ ለቀልድም ቢሆን የምንናገራትን እንደዶሮ እየለቃቀመ እሚወስድና እኛን ንጹሓን ዜጎችን ለእሥርና ለእንግልት እንዲሁም ለከፋ አደጋ የሚዳርግ የመንግሥት ተቋም ስለተተከለብን የልባችንን ብሶት በሚዲያ ወይም በአደባባይ መተንፈስ ይቅርና የሰላምታ ልውውጣችንም ወደፖለቲካ እንዳይዞርብን በመፍራት ምንጊዜም እንደተጨነቅን እንገኛለን፡፡ በዚህም ምክንያት ጸሐፍትና አስተያየት ሰጭዎች ስማቸውን ቢደብቁ ለመኖር ካላቸው ጉጉት አኳያ ነውና አንፍረድባቸው፡፡ የተጣለብን ገደብ እንዳንናገር ብቻ ሳይሆን እንዳናስብም ነው - ከከብቶች በእጅጉ ያነሰ ነጻነት ነው ያለን፡፡ ይህን ማን ያውቅልናል? የዚህን ሥርዓት ቁንጮ መለስ ዜናዊንስ አይደለምን ‹የአፍሪካ ተስፋ ወጣቱ ዴሞክራት፣ ለሌሎች አፍሪካውያን አርአያ የሚሆን የአፍሪካ ወካይ አንደበት፣...› እያሉ እኛን ለማናደድና በዴሞክራሲ ላይ ለማሽሟጠጥና ለማፌዝ በሚመስል አኳኋን ላለፉት 21 ዓመታት በየስብሰባቸው የሚጠሩትና በሰላማዊ ሠልፍ እሚያስጮኹበት? የገማ ዕንቁላልና ቲማቲም እሚያስወረውሩበት? አልፎ ተርፎም በድብቅ እያስታመመው የነበረውን የእርግማን ውጤት ልክፍቱን በወጣቱ ጋዜጠኛ አበበ ገላው የቃላት ኒኩሌር አረር እንደሂሮሽማና ናጋሳኪ አስደብድበው ሲያበቁ ለአልጋ ቁራኛና ስሙ ላልታወቀ አዲስ ኅልፈት እንዲዳረግ ያበቁት? እሱን ምን ጠቀሙት? እኛንስ ምን ጠቀሙን? እነሱስ ምን ተጠቀሙ? ሀገሪቱንስ ምን ጠቀሟት?  በኢትዮጵያ ውርደትና ብስቁልና የሚጎዳ እንጂ የሚጠቀም እንደማይኖር ብዙ ሳይመሽ ቢማሩ ለሁላችንም በበጀን ነበር፡፡ የአሸዋና የድንጋይ ክምርና የአስፋልት ንጣፍ የሀገርና የሕዝብ እውነተኛ ዕድገት መገለጫ እንዳልሆነ ማወቅ ከፈለጉ ወደ እያንዳንዳችን ቤት ጎራ ይበሉና በወያኔው ሰው ሠራሽ የኑሮ ውድነት እንዴት በመኖርና ባለመኖር መሀል እየተሰቃየን እንደሆነ ይመልከቱ፡፡ ከጊዜያዊ ግርግርና የሥልጣንና የሀብት ማጋበስ በስተቀር በቋሚነት ማንም በማይጠቀምበት የፖለቲካ አጀንዳ ምክንያት ሁሉም የሚጎዳበት ትዕይንት እየተሰናዳ ዐወድማውም እየተለቀለቀ እንደሆነ የሚመለከታቸው ወገኖች ልብ እንዲሉት በዚህ አጋጣሚ  በአፅንዖት ላሳስብ እፈልጋለሁ፡፡

እርግጥ ነው ይህ መልእክቴ ለስንቱ ይደርሳል የሚለው አንዱ ሥጋቴ ነው፡፡ ምክንያቱም ወያኔንና ደርግን የመሳሰሉ አምባገነን መንግሥታት ሕዝብንና አንጋችን በማይምነት ድቅድቅ መጋረጃ ሸኁረው መግዛትን እንደዋነኛ የአገዛዝ ሥልት ይጠቀማሉና ብዙው ዜጋ ለወቅቱ የዜናና የመረጃ መረቦች የቀረበ አይደለም፡፡ በዚያም ላይ በአሁኑ ወቅት የ‹ኢትዮጵያ› መንግሥት ከቻይና ሞራለቢስና ዓለምን እንደዘንዶ ሰልቅጦ ሊጨርስ የተዘጋጀ መንግሥት ጋር በመተባበር ከሞላ ጎደል ሁሉንም ወደኢትዮጵያ የሚገቡ የድረ ገፅና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ የዜና አውታሮችን ጠርቅሞ ዘግቷል፤ በልዩ መንገድ እየገባን የምንጠቀምባቸውን ሳይቀር እየዘጋቸው ነው፤ የሚገርመው ነገር ገና ትናንት የተጀመረችውን የአቤ ቶኪቻውን ሚጢጢዬ ብሎግ ሳይቀር ከነግንቦት ሰባትና ኢሣት ደርቦ ዘግቷታል - እንደሌሎች ጥቂቶች ድረ ገፆች በፕሮክሲም አናገኛትም፡፡ የሚገርም አፈና ውስጥ ነው የምንገኘው፡፡ እንኳን ዘንቦብሽ እንዲሉ ዱሮውንም ከ0.4 በመቶ በታች ከነበረው የኢንተርኔት ተጠቃሚ ከዚህ መቶኛም ውስጥ ስንቱ ፐርሰንት የኔን ይህንንም ሆነ የሌሎችን መልእክት የትና እንዴት ሊያገኝ እንደሚችል ስናስበው እጅግ በጣም አስጨናቂ በሆነ የኢንፎርሜሽንና መረጃ ዕጥረት ላይ መገኘታችንን እንረዳለን፡፡ አደንቁረውና በአፍዝ አደንግዝ የህንድ ይሁን የሱዳን አንደርባቸው አነፍልለው እየገዙን ናቸው ማለት እንችላለን፡፡ ብዙ ሰው ለዕለት ሆዱ ሲማስን እንጂ ሀገር ተጠበሰች ተቀቀለች የሚያገባው እንዳልሆነ ያህል ግዴለሽ የሆነ ይመስላል፡፡ ለዚህ አሳዛኝ የስሜት አልባነት ደረጃ ያበቁት በመጀመሪያ ደርግ ቀጥሎም በዋናነት ወያኔ መሆናቸው የታወቀ ነው፡፡ ቀዳሚው ሂሳቡ ተከፍሎታል፤ የነዚህም ሂሳብ እየተሠራ እንደሆነ መገመት አይከብድም፡፡ ብድራትን እንደየመክሊታችን ለሚከፍሉ ፈጣሪና ታሪክ ከወዲሁ ምሥጋናችንን እናቅርብ፡፡

ለማንኛውም ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም ይባላልና ከሕይወት ገጠመኜ በመነሳት የሁሉም ዘመናት ሰው መሆን በሚቻልበት ብቸኛ መንገድ ላይ ለሚመለከታቸው ወገኖቼ የተወሰነ ግንዛቤ ባስጨብጥ ደስ ይለኛልና ወደዚያው ላዝግም፡፡

በአፄ ኃይለ ሥላሤ ዘመነ መንግሥት መጨረሻ አካባቢ በወጣትነት ዕድሜየ መቋጫ ገደማ የአፄውን የንጉሠ ነገሥት መንግሥት በደኅንነት (Intelligence) ሠራተኝነት እንዳገለግል ከወዳጆቼ ተጠቁሜ ብዙም ሳላንገራግር ገባሁ፡፡ የኔ አገልግሎት መነሻውም ሆነ መድረሻው ሀገርና ሕዝብ መሆን አለባቸው ብዬ ስለማምን በብዙ ነገሮች አሠራር ደስተኛ አልነበርኩም፡፡ በዚያም ሳቢያ ከአለቆቼም ሆነ ከሌሎች ባልደረቦቼ ጋር ስምም እንዳልነበርኩ ይታወሰኛል፡፡ እኔ የማምነው ሀገርንና ወገንን በታማኝነት ማገልገልን እንጂ አልጋና ዙፋንን መጠበቅ የባለ አልጋው ወይም የባለሥልጣኑ ድርሻ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ግን በአፄውም ሆነ ከለውጡ በኋላ ለተወሰኑ ዓመታት ባገለገልኩት በደርጉ ሥርዓቶች የነበሩ የፀጥታና የደኅንነት ተቋማት ዋና ትኩረታቸው ከሀገር ይልቅ ሥልጣን ጥበቃ ሆነ፤ በዚያም ምክንያት ተቋማቱ በሕዝብ ዘንድ ተጠሉ፤ ተነጠሉም፡፡ እነዚህን ተቋማት ለማንቀሳቀስም ለልማትና ብልፅግና ወይም ድህነትን ለማጥፋትና ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር መዋል የነበረበት እጅግ ብዙ የሀገር ሀብትና ንብረት ለወንበር ጥበቃ ብቻ ይባክን ያዘ - ለዚህ የወንበር ጥበቃ የወጣውንና አሁንም የሚገፈገፈውን የሀገር አንጡራ ሀብት በአንድ በኩል ከሰሞኑ የሎንዶን አሎምፒክ ወቅታዊ ክንዋኔ አንጻር አንድም ደረጃውን የጠበቀ የእግር ኳስ ስቴዲየም (የኦሎምፒክ መንደሩ ቀርቶብን) አለመኖሩን በሌላ በኩል ስናስብ በዕድላችን መጥፎነት እንቆጫለን፤ ለሀገር ልማትና ዕድገት ሳይሆን ለሥልጣናቸው ይበልጥ ቀናኢ በሆኑ የሀገር መሪዎች መወረራችንም እንደ እግር እሳት ይፈጀናል(የአንድ ቀን ጦርነት ወጪና የአንድ ቀን የሰለላ ወጪ ልማት ላይ ቢውሉ ብላችሁ እስኪ ለአፍታ አስቡት)፡፡ በተለይ ላለፉት ዐርባ ዓመታት በአጓጉል የሀገር አስተዳደርና ብልሹ አመራር ሳቢያ በሚፈጠሩ የውስጥና የውጭ ጦርነቶችም ምክንያት ሀገርን ሊያሳድግና እንደእኩዮቻችን ከፍ ባለ ወንበር ሊያስቀምጠን ይችል የነበረ እጅግ ብዙ ጥሪት በከንቱ እየወደመ እሳት ውስጥ የገባ ቅቤ ሆኖ አለመላው ቀልጦ መቅረቱን ተያያዘው - ሀገሪቱ ባለቤት የሌላት እስክትመስል ድረስ፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው እንግዲህ አምባገነን መንግሥታቱ ከሀገር ይልቅ ወንበራቸውን በማስቀደማቸውና የእልህ ፖለቲካ በማራመዳቸው፣ ያንን ገታራና ሀገርንና ሕዝብን የናቀ የአስተዳደር ዘይቤያቸውን ለማስቀጠልም የሀገርን ሀብት እንደልባቸው ሊያዙትና ሊጠመዝዙት የሚችሉት የደኅንነትና የጦር መዋቅር በመገንባት ነው፡፡ እነሱው ራሳቸው አንዱ የገነባውን ሌላኛቸው እያፈረሱና በአምሳያቸው ሌላ የሚመቻቸውን ቀርጸው እየተኩ ሕዝብን ማዋረዱንና ሀገሪቱን ለባዕዳን የእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ማስረከቡን ሥራየ ብለው በመያያዛቸው ይሄውና አሁን ለምንገኝበት የመከራ ዘመን ተዳርገን አለን - መኖር ተብሎ፡፡

ይህ ዓይነቱ አገዛዝ መቆም ካለበት ወደኅሊናው ተመልሶ እንደወያኔ በጉልበት ወደሥልጣን ለሚመጣ የጫካ ወሮበላ ብቻ ሳይሆን ከሕዝብ ፈቃድ ውጪ በማጭበርበርና በማታለል ወይም ኮረጆ በመገልበጥ ወደሥልጣን ለሚመጣ ማናቸውም ኃይል በቀላሉ የማይንበረከክ የደኅንነት ተቋምና የመከላከያ ሠራዊት እንዲኖረን ያስፈልጋል፡፡ ያደጉ ሀገሮችን የሥልጣን አያያዝ ስንመለከት እኛ ምን ያህል የኋሊት እንደቀረን እንረዳለን፤ መለስ ዜናዊ ሥልጣን ከያዘ ወዲህ በዩ ኤስ አሜሪካና በዩ ኬ፣ በጣሊያንና በጃፓን ስንትና ስንት የሀገር መሪዎች እንደተለዋወጡ ስንታዘብ ክፉኛ የመረገማችን ሸክም ይሰማናል፡፡ አንዳንዶቻችንም በዚህ አጋጣሚ በእጅጉ ልናፍርና በኢትዮጵያዊነታችን አንገታችንን ልንደፋ እንገደዳለን፡፡ በሰዓታት ውስጥ በተከናወነ የምርጫ ክንውን ውጤት ሳቢያ ቡሽ ለኦባማ፣ ብራውን ለካሜሮን ቤተ መንግሥቱን አስረክበው ጓዜን ጨርቄን ሳይሉ በሕዝብ ፊት ውልቅ ብለው ሲወጡ ስናይ እኛ ላይ የተጫነውን መርግ ካለሞት እንደማንገላገለው በቁጭት እንገነዘባለን፡፡ ይህን እስከመቅኒያችን ድረስ ዘልቆ የተጣባንን የሥልጣን ሱስና አራራ የምንከላባበት አንዳች የወል መፍትሔ ካላገኘን ስደቱም፣ የኋሊት ጉዞውም፣ ጦርነቱም፣ እንግልቱም፣ እሥራትና ሞቱም ... በባሰ ሁኔታ ይቀጥላል፡፡ ለዚህ ደግሞ እንዳሁኑና እንደእስካሁኑ ‹ፖለቲካንና ኮረንቲን በሩቅ› በሚለው የአድርባዮችና የፈሪዎች ሽሽት ሳይሆን በቆራጥነትና በያገባኛል የባለቤትነት ስሜት በጋራ መረባረብ አማራጭ የሌለው የወቅቱ ጥሪ ነው፡፡

ነገርን ነገር እያነሳብኝ ወደ ዋናው ጉዳይ ሳልገባ ዘገየሁ፡፡ ይቅርታ፡፡

በሚገባ የማውቃቸውን ሦስቱን የአገዛዝ ሥርዓቶች የደኅንነትና የፀጥታ መዋቅሮች በሚመለከለት ብዙ ማለት እችላለሁ፡፡ በአጭሩ ግን ከፍ ሲል ለመጠቆም ሞክሬያለሁ - ያም ተቋማቱ ከሀገርና ከሕዝብ ጥቅምና ፍላጎት ይልቅ ሥርዓቶቹን ደግፎና ቀጥ አድርጎ ለዘላለም በሚመስል ሁኔታ ለማኖር መሞከር ነው፡፡ ይሁንና በዚህ ሂደት በተለይ የአሁኑ መንግሥት ዋና ተዋንያን ማለትም  የአቶ ጌታቸው አሰፋ የደኅንነት ተቋምና የሣሞራ የኑስ  የ‹ሀገር› መከላከያ ሠራዊት እንዲሁም የ‹ወርቅነህ ገበየሁ› የፖሊስ ሠራዊት በውል ሊገነዘቡት ያልቻሉትና ምናልባትም የማይችሉት አንድ መሪር እውነታ አለ፤ ይሄውም ማንም ሰው ወይም ተቋም አንድን ሰው ወይም ተቋም በሕይወት ጠብቆ ሊያቆየው የሚችልበት የጊዜ መጠን ያለው መሆኑንና ያ ጊዜ ሲደርስ ግን ሁሉም ነገር ባልታሰበ ወቅትና ባልታሰበ ሁኔታ ባልተጠበቀ ምናልባትም በተናቀ ኃይል ተንኮታኩቶ ሊወድቅ የመቻሉን ታሪካዊ ሃቅ ነው፡፡ ለዚህ ብዙ መሄድ አያስፈልግም ፤ ጎልያዱ ደርግ ደቃቃዋን ወያኔ ለዓመታት ሲንቅና ስሟን እንኳን በቁስ ይጥራው እየሸፋፈነ ላይጠራት ሲጠየፍ ባጅቶ በመጨረሻው መጨረሻ ግን በርሷው ምሪትና ምንደኞች ይላቸው በነበሩ የውስጥ አርበኞች እገዛ እንዲሁም በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ሻጥሮች በማያንሠራራ

መልኩ - በወያኔያዊ የዕብሪት አነጋገር - አከርካሪው ተመትቶ ግብኣተ መሬቱ ዘመድ ወዳጅ ባልተገኘበት የሎንደኑ ጉባኤ ላይ ተፈጽሟል፡፡ የናቁት ወንድ ማስረገዙ የነበረ ነው፤ ‹የጠሉት መድረሱ፣ የፈሩት መድረሱ›ም የነበረና ያለ ነው፡፡ ጉንዳን እንኳን ባቅሟ ጀግና ነኝ የሚልን ባለጓንዴና ባለሞይዜር ነፍጠኛ እሰው ፊት ሱሪ ታስወልቃለች፡፡ ለዚህም ነው ታላቁ መጽሐፍ ‹ኢ(ይ)ድህን ንጉሥ በብዝኃ ሠራዊቱ› የሚል፡፡ ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም ለማለት ነው፤ እውነት ነው - ከእርሱ የመጣን መርገምም ይሁን በረከት የሚመልሰው እንደማይኖር ከበቂ በላይ ማስረጃዎችንና መረጃዎችን በመጥቀስ ማሳየት ይቻላል፡፡ ይህ የማይታያቸው በዱባ ጥጋብ ካለ(በቂ) ስንቅ መዝመት የሚቃጣቸውና በእጃቸው የገባን ወርቃማ ዕድል በአግባቡ መጠቀም የማይችሉ ወያኔን መሰል ደናቁርት ጠመንጃ አምላኪዎች ናቸው፡፡ ጉልበተኝነት እስከወዲያኛው ቢያዋጣ ኖሮ በምሥራቅ አፍሪካ ቀርቶ በመላዋ አፍሪካ ሳይቀር (ከደቡብ አፍሪካና ምናልባት ከግብጽ በስተቀር) እንደሙብረቅ ነጎድጓድ የሚያስገመግምና ዝናው ብቻ የሚያርድ ልዩ ጦር ገንብቶ የነበረው የመንግሥቱ ኃ/ማርያም ደርግ ማንም ሳይነካው ዝንታለሙን በኖረ ነበር፡፡ ሁሉም የዓለም ነገር ከንቱና የከንቱ ከንቱ ነው - ንፋስንም እንደመከተል የሚመስል ከንቱነት - እንደመጽሐፉ፡፡ እናም የጊዜ ጉዳይ እንጂ የስለላና የጦር መዋቅሮች ያዳኑት አምባገነን መሪ በዓለም ኖሮ አያውቅም፤ ዛሬ የሚጀመርም አይሆንም፡፡ እርግጥ ነው - ዘመኑ እስኪደርስ የሕዝብ ዕንባ እስኪያርግና በፈጣሪ መልስ እስኪያገኝ ፣ ለፍትህ ሲጮሁ አለፍትህ የተጨፈጨፉ ዜጎች ደምና አጥንት ወደሰማይ አርጎ የፈጣሪን አጸፋ እስኪያገኝ፣ በቂም በቀል ታስረው የመፈቻቸውን ጊዜ በኤሎሄ እየጠየቁ ያሉ ወገኖች ጸሎት ወረፋው ደርሶ መልስ እስኪያገኝ ድረስ ባለው ወርቃማ ዘመናቸው ወንጀለኛ አምባገነኖች በወንጀለኛ ሕጎቻቸውና በወንጀለኞች ተቋሞቻቸው አማካይነት ብዙ ነገሮችን ሊያከናውኑ መቻላቸው የታወቀ ነው፡፡

እኔ በአፄውና በደርጉ የደኅንነት ተቋም እንደመሥራቴ  ለምን እስካሁን በሕይወትና ከሕዝብ ጋር ልኖር ቻልኩ? ለምን አልታሰርኩም? ለምንስ አልተገደልኩም? ከሕዝብ ጋርስ ለምን አልተቃቃርኩም? ልጆች ባደረ የአባታቸው የወንጀል ሥራ ሳያፍሩ አንገታቸውን ቀና አድርገው መሄዳቸው ያኮራኛል፡፡ በመሠረቱ እኔ አስብ የነበረው ስለልጆቼ አንገት መቃናት ወይ ማጋደል አልነበረም፡፡ ትልቁ ነገር የኔ ሥራ ሕዝብን ይጠቅማል ወይንስ ይጎዳል? ከሚል የሚመነጭ ነበር፡፡ የየዕለቱን ሥራየን ማታ ስተኛ እገመግም ነበር፡፡ በውነቱ እንኳንስ በደኅንነት መዋቅር በሌላ ቦታም የሥልጣን ነገር መጥፎ ነው፤ አንዳንድ ነገር ለማግኘት ያጓጓል፤ ተቀናቃኝን ለመበቀል ምቹ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል… ነገር ግን ሕይወት ፈተና እንደመሆኗ ቁርጠኛ አቋምን በመያዝ ለኅሊናና ለእውነት ተገዝቶ ፈተናን መቋቋም ይቻላል፤ ከባድ ሊሆን ቢችልም ጨርሶውን የማይቻል ግን አይደለም፡፡ ፈተናን መቋቋም ደግሞ አንድን ሰው ብቻ ሳይሆን ማኅበረሰብንና ከፍ ሲልም ሀገርን ይጠቅማል፡፡

አሁን ከፊታችን የተጋረጠ ኢትዮጵያዊ ፈተና አለ፡፡ ይህ ፈተና የሁላችንንም ጤናማ አእምሮና ታጋሽ ስብዕና ይጠይቃል፡፡ በተለይ ወጣቱ ጌታቸው አሰፋና አባላቱ እንዲሁም የመከላከያና የፖሊስ ባልደረቦች ብዙ ነገር ይጠበቅባቸዋል፡፡ እያወራሁት ያለሁት ስለግለሰብ ጤንነት ወይም ስለአንድ ሰው መሞት አይደለም፡፡ አቶ መለስን ለማጣቀስ ፈልጌ ነው፡፡ አቶ መለስ ፈጣሪ መልስ ሰጥቶታል፡፡ ከዚህ አስገራሚ ሁኔታ ሁላችን ብዙ ልንማር ይገባል፡፡ ጦሩንም ፖሊሱንም መከላከያውንም ከሕዝብ ጋር ደም ያቃባው እርሱ ነበር፡፡ እርሱ ደግሞ እንደማንኛውም ሰው ሊሞት እንደሚችል ፈጣሪ እያሳየን ነው፡፡ እንዲያውም ከሞቱ ይልቅ አሟሟቱ ብዙ ግንዛቤን ያስጨብጠናል፡፡ በመሠረቱ በአሁኒቷ ቅጽበት ስለመለስ የጤና ሁኔታ ማለትም ይሙት ይዳን በውል አላውቅም - ባይሞት ግዴለኝም ብዬ ግን ማንንም ልዋሽ አልፈልግም፤ የሞራልና የሃይማኖት ጥያቄ እዚህ ላይ አግባብነት የለውም፡፡ ክርስቶስ ስለከሃዲው ይሁዳ ሲናገር ‹የሰውን ልጅ በመሳም አሳልፎ የሚሰጥ (ቀድሞ ባይወለድ ከተወለደም) በአንገቱ የወፍጮ መጅ ታስሮ ወደጥልቁ ባሕር ቢወረወር ይሻለዋል› እንዳለው ይህ ኢትዮጵያን ከነሕዝቧ መቀመቅ ያወረደ ሰው እንዳይሞት መጸለይ ወይም ለዚህ ክፉ ሰው ራሮትን ማሳየት ይህን ከፍ ሲል ክርስቶስ የተናገረውን ቅዱስ ቃል በቀጥታ እንደመቃወምና ከሃይማኖት እንደመውጣት አድርጌ እቆጥረዋለሁ - ነፍሱን ይማር ከጨዋ ሃይማኖተኛ የሚጠበቅ ነው፤ያኑርልን ግን ከጥቅም ተጋሪና ከዓላማ ሸርከኛ ብቻ የሚደመጥ መሆን አለበት፡፡ እነዚያም አይፈረድባቸውም - እስትንፋሳቸውና የፈጣሪን ያህል የሚያመልኩበት ጣዖታቸው ነበርና፡፡

በአሁኑ ወቅት ሩህያው ከሥጋው ተለይታ ልትወጣ ባይቻላትም እንኳን የተያዘበት አኳኋን ሌልኛ ስለመሆኑ ሰምቻለሁና እንደማይተርፍ በከፍተኛ ደረጃ እገምታለሁ፡፡ የፈጣሪን ፍርድ ስናየው የሚያስገርመን ይህን አናት አናታችንን እንደእባብ ሲቀጠቅጠንና ሲያስቀጠቅጠን የነበረን ሰው በተራው እርሱም አናቱን በጅንፎ የካንሰር ዱላ መቀጥቀጡ ነው፡፡ ይህ በውነቱ የሚያስገርም ነገር ነው፡፡ የሥቃዩን መብዛት፣ የጣሩን ጥናት ስንታዘብ የክፉ ሥራ ውጤት ምን ያህል አስደንጋጭ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ ይህ ሁኔታ ወደራሳችን ውስጥ ተመልሰን ራሳችንን በዐይነ ኅሊናችን እንድንቃኝ የአርምሞ ጊዜ ይሰጠናል፡፡ የ‹ፌዴራል› ሠራዊቱ፣ ኳስ ሊያነሳ ወደመሬት ያጎነበሰን የ15 ዓመት ዕድሜ ታዳጊ ደረቱን በጥይት የመታው ለመለስ የሥልጣን ዕድሜ መራዘም ነበር - ከዚያን አሰቃቂ ጊዜ በኋላ መለስ ስንት ዓመታትን ኖረ? በደፈናው ምንም

አልኖረም፤ መለስ መቼም ቢሆን ኑሮን ኑሮ አያውቅምና - እንደ አንበሣ በብረት ዘብ ዕድሜ ልክን ታጅቦ መኖር፣ በተጣመመ የፖለቲካ አመራር ሀገርንና ሕዝብን እያስለቀሱ በዕንባና በደም በጨቀዌ ቤተ መንግሥት ውስጥ መኖር ሰቀቃ እንጂ ኑሮ ሊባል አይችልምና መለስ በዚህች ምድር ኖረ ከማለት ይልቅ እየተሰቃዬ አሰቃዬ ማለት ይቀላል - በዚያኛውም የሚኖር ስለመሆኑ ማንም እርግጠኛ መሆን የሚችል አይመስለኝም፡፡ እንደ ዳላይ ላማውያን የቡድሂስቶች አስተሳሰብ ዳግመኛ ዐይጥና ድመት እየሆነ መጥቶ የነፍሱን ጥራት ከዘጠኙ ዳግም-ልደቶች በአንደኛው ካላስመሰከረ በስተቀር መለስ በቁሙ የሞተ ፍጡር ለመሆኑ እማኝ መቁጠር ሳያስፈልገን የኛን የብዙዎቻችንን ቀላልና ያልተወሳሰበ ሕይወት በማየት መረዳት እንችላለን፡፡ እንደምንም ኖረ እንበልና ግን ከዚያን የጨነገፈ ሕዝባዊ ምርጫ ወዲህ ይህን ዓመት ሳይጨምር 6 ዓመታትን ኖሯል- መኖር ከተባለ፡፡ በነገራችን ላይ በመለስ መኖር የተጠቀመ ብቸኛ ነገር ቢኖር አንግቦት የተነሳው ዓላማው ብቻ ነው፡፡ ያ ረቂቅ ጎላዌ - ከመለስ ተፈጥሮ ጋር በቀጥታ የተቆራኘው <u>**ሕዝብን እርስ በርስ የማናከስና የማፋጀት በውጤቱም  ሀገርን መቅኖ የማሳጣት ሰይጣናዊ ዓላማ**</u> በተወሰነ ደረጃ ተሳክቷል፤ ለዚህም ነው ከመለስ ይልቅ በሰውኛ ዘይቤ መለስ ይዞት የተነሳው ዓላማ ይበልጥ ተጠቅሟል - ኖሯል - ለማለት የደፈርኩት፡፡ እርሱም በሂደት እንደአጋፋሪው መለስ በቅርብ ይሞታል- ዓላማው፡፡  ለነዚህ ሟቾች ጋሻጃግሪ ሆኖ እስከመጨረሻው ከሕዝብ አንጻር መቆም ደግሞ ታሪክ ይቅር የማይለው ጥፋት ነው፡፡ እናም ከሚሞት ይልቅ የማይሞትን ማገልገል እንደሚገባ ሁሉም የፀጥታውም ሆነ የስለላው ተቋማት ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ ያኔ ነው የዘላለም ኗሪ መሆን የሚቻለው፡፡ ያኔ ነው ሥርዓት በተለወጠ ቁጥር በአዩኝ አላዩኝ እየተደበቁ በሰቀቀን መኖር የሚቀረው፤ ያኔ ነው ‹የእነእገሌ አባት እኮ እንደዚህ የመሰለ ማፈሪያ ታሪክ በመሥራቱ ነው ልጆቹ አንገታቸውን አቀርቅረው በሀፍረት የሚኖሩት› ከመባል የምንድነው፡፡ ያኔ ነው ‹እገሌ ለሆዱና ለጎሣው ሲል እንዲህ ያለ ብልግና ይፈጽም ስለነበር ነው ይህን ያህል ዓመት እሥራት የተፈረደበት› ከመባል የምንድነው፡፡ ያኔ ነው በየሥርቻው ሳንሸጎጥ በሠራነው አኩሪ ሕዝባዊ ታሪክ ምክንያት በኩራት በሕዝብ ፊት የምንመላለሰው፡፡  … ልብ ያለው ልብ ይበል፡፡ ጊዜው ሲደርስ እንኳን ሰው ተራሮችና ወንዞች፣ ድንጋዮችና አለቶች ይናገራሉ - የሚሰማ ይስማ፡፡ የመጥምቁ ዮሐንስ የዘመኑ ቀርቧል የበረሃ ስብከት እየተስተጋባ ነውና ከሽፈትንበት ዓለም ተመልሰን ወደየጎሊና ጓዳችን እንግባና ራሳችንን እንፈትሽ፡፡ እገሌ ከእገሌ ሳንባባል ሁላችንም - የቆምን የመሰለን ሳንቀር! የወደቀማ ይታዘንለታል፡፡ ምንስ ሲቀርበት - አንዴውን ወድቆ የለም?

አሁን ደኅንነቱና ጦሩ እንደኔ እንደቀድሞው የፀጥታው ተቋማት ሠራተኛ ባልደረባቸው ከብዙ ነገር ሊጠበቅ ይገባዋል፡፡ ከተደጋጋሚ ስህተትም ባፋጣኝ ወጥቶ ሕዝባዊ ደጀንነትን ማረጋገጥ ይኖርበታል፤ እንደተሳሳተና እየተሳሳተ የሚኖር ጤናማ አእምሮ የሌለው ሰው ብቻ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ አጋጣሚ ብዙውን ጊዜ አይገኝም፡፡ መለስ በአሁኑ ወቅት አድራሻው አይታወቅም፡፡ ምናልባትም እስከወዲያኛው ተሠውሮ ሊሆን ይችላል፡፡ እርሱ ይሙትም ይዳንም የራሱ ጉዳይ፡፡ ሀገርና ሕዝብ ግን ወደየትም ሊሠወሩም ሆነ ሊሞቱ አይችሉም  - ዘላለማዊ ናቸው፡፡ እኛ ደግሞ ከግለሰብ አምላኪነትና አገልጋይነት ወጥተን ለሕዝብ አንድነትና የጋራ ደኅንነት ዘብ መቆም ይኖርብናል፡፡ እስካሁን የተታለልነው ይብቃንና ከአሁን በኋላ ለራሳችንና ለልጅ ልጆቻችን እንዲሁም ለሀገር የማይሞት ታሪክ እንኑር፡፡ እርግጥ ነው የተለያዩ እንቅፋቶች ሊጋረጡብን ይችሉ ይሆናል፡፡ ከሁሉም ነገሮች ግላዊም ይሁን ቡድናዊ ለውጥን ማምጣት ከባድ ነው፡፡ እንደማስበው የዘመኑ ልክፍት የሆነው በዘርና በጎሣ እየተቋጠሩ የትግል ዓላማ ውስጥ መግባት የተወሰነ ግን ጊዜያዊ አእምሯዊ አለመረጋጋትን ማስከተሉ አይቀርም፤ ይህ ደግሞ የመለስና ግብረ አበሮቹ የጥቂት አሥርት ዓመታት ደንቃራዊ ሥራና መፍትሔ ሥራዩን በቀላሉ የማያገኙለት ፖለቲካዊ ትብታብ ነው፡፡ ነገር ግን ወደጤናማ ኅሊና መመለስ ለሁሉም ሃይማኖታዊም ሆነ ዘውጋዊ ችግሮቻችን መፍትሔ ማግኘት የመጀመሪያው እርምጃ ነው፡፡ የምንሰግድለትና ትዕዛዙን እንደወረደ ተቀብለን በመፈጸምና በማስፈጸም ሕዝብን ስንገርፍለት፣ ስናስርለትና ስንገድልለት የነበረው አቶ መለስ ዜናዊ ላይመለስ ጥጉን የያዘ ይመስላል፤ ይህን መልካም አጋጣሚ ለመለወጣችን እንደዓይነተኛ ግብኣት ልንጠቀምበት እንችላለን፡፡ ሃዲያዎች ‹የመጀመሪያው ቂጣ ቢያር ሁለተኛው አያርም› ይላሉ፡፡ ከአሁን በፊት ልባችን በዚህ ዘረኛ አገዛዝ ላይ ሊያምጽ የከጀለበት ወቅትና ሁኔታ ይኖር ይሆናል - ያ በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሳካልን አልፏል፡፡ አሁን ግን ከምር ከተነሳን ይህ አጋጣሚ ሊያመልጠን አይገባም፡፡ ማየት የሚኖርብን ሥራ ላይ ሳለን በቢሯችን ግድግዳ ላይ ተገሽሮ የምናየው የመለስ ምሥል ሳይሆን የልጆቻችንና የኛ የወደፊት ዕጣ ፋንታ መሆን አለበት፡፡ ለእንጀራ እንደሆነ አትጨነቁ፤ አንድ እንጀራ አታጡም - ብታጡም ለምናችሁ ብሉ፤ በወንጀል ከሚበላ ጮማ ቁርጥ ይልቅ ተለምኖ የሚቀመስ ንፍሮና ቆሎ ይሻላል፡፡ ደግሞም የነሦርያን፣ የነሊቢያን፣ የነቱኒዝያን፣የነግብጽን … ታምቆ ያልቀረ ታሪክ አጢኑ፡፡ የነዚያን ሀገሮች ሕዝባዊ አመፆችና የለውጥ ማዕበላት ጦሩና የደኅንነት ተቋሞቻቸው አግደው አላስቀሩም - መፍጨርጨራቸውና የታሪክ ትዝብት ውስጥ መግባታቸው ግን አልቀረም፡፡

ይሄ አቶ መለስ ከመጋረጃ በስተጀርባ ሆኖ ሀገር እያስተዳደረ ነው ወይም ሀገራትን እያስታረቀ ነው የሚባለው ነገር ከጨዋታ የሚያልፍ አይደለም፡፡ ነገሩ ‹ጽድቁ ቀርቶብኝ በቅጡ በኮነነኝ› ይሉትን ዓይነት  ነው፡፡ ማስታረቁ ቀርቶበት ከ50ዎቹ የ‹ሱባኤ› ቀናት ውስጥ ባንደኛዋ ቢያንስ ያን ሥራዬ ቤታዊ አሸሙሩን በሬዲዮ ባሰማን የኅሊና ዕረፍት ባገኘን፣ በመሪ ዕጦትም

መርከባችንን የውቅያኖስ ወጀብ ባላንገላታብን ነበር፡፡ እርግጥ ነው - በአሁኑ ወቅት ሰውዬው ለይቶለት ይሙት ወይም እንደእስራኤሉ የቀድሞ መሪ እንደኤሪየል ሻሮል በጣር ሰመመን ውስጥ ይሁን ለይቶ ማወቅ ይከብዳል፡፡ በርግጠኝነት መናገር የምንችለው ግን ከፍ ሲል ለማየት እንደሞከርነው መለስ ከእንግዲህ ወዲያ በእስካሁኑ ሰይጣናዊ ግርማ ሞገሱ ወደሥልጣን ይመለሳል ማለት ዘበት ነው - የበረከት ቅዠት ካልሆነ በስተቀር፤ ከመስከረም በፊት ወደሥራ ይመለሳል የተባለውንም ልናይ ነው፡፡ ‹ሽልም ከሆነ ይገፋል፤ ቂጣም ከሆነ ይጠፋል፤ አይደል የሚባል? [ልታምኑበት የማይጠበቅባችሁ መረጃ ላካፍላችሁ መሰለኝ፡- ከሱዳን ዐይኗ እንዲጠፋ ተደርጎ የመጣችው ጥቁሯ አህያ ሞታለች ወይም በመሞት ሂደት ላይ ናት፤ በሜክሲኮ አደባባይና በሌሎች አካባቢዎች ሌሊት ሌሊት በከበሮና በማሲንቆ በሰሜነኛ ሥልት እየተጨፈረ ይደረግ የነበረው ሟርትና ደንቃራም ከእንግዲህ አበቅቴው ስለደረሰ አይሠራም፡፡ ማንኛውም ጅምር ማለቂያ አለውና ይህ የወያኔዎች በሺዎች ዓመታት አንዴ ሊያጋጥም የሚችል የውሽንፍርና የመከራ ዘመንም ልክ እንደነዮዲት ጉዲትና እንደነአህመድ ግራኝ የጥፋትና የቅጣት ዘመቻዎች ሁሉ ወደ ታሪክ መጋዘን ገብቶ ሊቆለፍበት የቀረው ጊዜ በጣም አጭር ነው - ለካንስ ስለሚመጣ ነገር እንደመናገር ያለ ቀላል ነገር የለም ጎበዝ! … ] በዚህች በቅንፋዊ አስተያየቴ ወያኔያውያን ደስ ይበላችሁ - ማስተዛዘኛየ - ይሁነኝ ብዬ ወጪ ያደረግኋት ናት - ለእናንተ፡፡

እናም ውድ የሥራና የሙያ ባልደረቦቼ - አደራችሁን ተጨማሪ ቆሻሻ ታሪክ ከመሥራት ተቆጠቡና በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የበደላችሁትን ሕዝብ ለመካስ ቆርጣችሁ ተነሱ፡፡ በመንግሥት ሠራተኝነታችሁ እየታዘዛችሁ ብዙ መጥፎ ነገሮችን ከአሁን ቀደም ሠርታችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ወደ መልካም መንገድ ለመመለስ ቀነ ገደብ የለውምና ዛሬና አሁንም ቢሆን ወደየጎሊናችሁ ተመልሳችሁ በቅርብ ሕይወት እንደሚዘራ የሚጠበቀውን ሁለንተናዊ የነጻነት ትግል ተቀላቀሉ፡፡ ከእኔ ከወንድማችሁ - ለብዙዎቻችሁ ደግሞ ከአባታችሁ - ብዙ የምትማሩት ነገር አለ፡፡ ሁሉም ነገር እንደሚያልፍ ተረድቻለሁ፤ ወጣትነት ያልፋል፤ ውበት ይረግፋል፤ ሀብት ይጠፋል፤ ሰውነት ይከዳል፤ ዝናም ቢሆን ይደበዝዛል፡፡ አሁን እኔን ብታዩኝ የዛሬ 35 ዓመት ከተነሳሁት ፎቶ ጋር አስተያይታችሁ ዳግም የተፈጠርኩ ያህል ልትገምቱ ትችላላችሁ፤ የያኔው እኔና የአሁኑ እኔ የሰማይና የምድርን ያህል እንራራቃለን፡፡ ይህ ነገር ለእናንተ አዲስ ሆኖ አይደለም፡፡ ነገር ግን እንዲህ በቁም ሳይቀር ለሚረግፍ ዓለም ብዙ መጥፎና ተንኮል መሥራት እንደማይገባ ለማስታወስ ነው፡፡ እርግጥ ነው - በደኅንነት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ሞራልና ሰብአዊነት ዕርም መሆናቸውን አውቃለሁ - ጭካኔና ኢምክንያታዊ ክንውኖች እንደሚዘወተሩም እረዳለሁ፡፡ ያን ማድረግ ግን ከሀገር ጎልውናና ከኢኮኖሚክ ኢንተሊጀንስ አንጻር በሚዘረጉ የኢንተሊጀንስና የካውንተር ኢንተሊጀንስ ዓለማቀፋዊ እንቅስቃሴዎች ላይ እንጂ የገዛ ወገንን በማጥመድ ለማሰቃየት እንዳይሆን መጠንቀቅ ተገቢ ነው፡፡

ከሁሉም የማያልፈው ታዲያን የሚሠሩት ዕኩይም ይሁን በጎ ሥራ ነው፡፡ በየትኛው መንገድ መታወስ እንደምንፈልግ የምንወስነው ደግሞ እኛው ራሳችን ነን፡፡ አምባገነንን በጭፍን እያገለገሉ በሚገኝ የሕዝብ ገንዘብ ሕዝቡን ራሱን ባልተወለደ አንጀት መግረፍና የዕንባ ጎርፍ በሚያስከትለው የቅጣት በትር ወደታሪክ አራሙቻነት መለወጥ ይሻላል ወይንስ ሰው እንደሆነው ሆኖ የተገኘውን እየተቃመሱ ለሕዝብና ለሀገር ወገንተኝነትን ማሳየት ይሻላል? ምርጫው የእናንተ ነው፡፡ እስካሁን - አንዳንዶቻችሁ - በዘር ልጓም አንገላችሁን ተቀይዳችሁ የሠራችሁት መጥፎ ነገር ሊኖር ይችላል፤ አሁን የሚጠቅመው ያን ማባባስ ሳይሆን ንስሃ ገብቶ ማለትም ተጸጽቶ ዳግመኛ ወደጥፋት ላለመሄድ መወሰን ነው፡፡ እንጂ በካፈርኩ አይመልሰኝ የዘረኝነት አሮንቃ ውስጥ እየተንቦራጨቁ ተጨማሪ ጥፋት ለመሥራት መነሳት ጤነኝነት አይደለም፤ የታሪክ አጸፋዊ ቅጣትም የምትችሉት አይሆንም፡፡ ሳያውቁ የሚያጠፉ አመክሮ ሊኖራቸው ይችላል - የሚሠሩትን በማወቅ ከአጥፊዎች ጋር ሆን ብለው የሚተባበሩ ግን ዋጋቸው ከአለቆቻቸው ጋር የተካከለ ነው፡፡ እዚህ ላይ ልብ ማለት የሚገባን ነገር ትናንት በሆንነው ነገር ማፈር እንደሌለብን ነው፡፡ መለወጥ ያለ ነገር ነው፡፡ በሃይማኖት መጽሐፍ እንደተቀመጠው ሳዖል የተባለው የኋለኛው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቶሳውያንን እያሳደደ ይገድል ነበር፡፡ በኋላ ላይ እውነቱ ሲገለጥለት ግን ‹ክርስቶስ ሆይ፣ ምን እንዳደርግ ትፈልጋለህ?› በማለት ባደረገው ነገር ሁሉ ከልቡ ተጸጽቶ የተዋጣለት ወንጌላዊና የክርስቶስ አገልጋይ ሆኗል፡፡ እናንተም ከልብ ከተለወጣችሁ ሕዝቡን ለመካስ አልረፈደባችሁም፡፡ ይሉኝታ ደግሞ እሚያምረው መጥፎ ነገርን ለማድረግ በሚጠየፉበት ወቅት እንጂ የተቀደሰ ነገርን ላለመቀበል በሚደረግ መግደርደር አይደለም፡፡ የኔ ምክር ያጥፋችሁ - የሕዝቡን ብሶትና እሮሮ አድምጡ፤ ሕዝቡ የሚያለቅሰው ዕንባ አልቆበት ዐይኑ ደም እያዠ ነው፡፡ የሕዝቡ ጸሎት ሥራውን ሠርቶ በልጃገረዶች የጭዳ ግብር የሰው ሥጋና ደም ይቋደስ የነበረውና በብሩክታዊት ወር ተራ ላይ መለኮታዊ ብያኔውን ያገኘው በመለስ ዜናዊ ውስጥ መሽጎ የሚያምሰን ደራጎን በመግረሬፀር የብፁኣን አባቶች ጸሎት አናቱ ተመትቷልና ከእንግዲህ አብዛኛው የዳገቱ መንገድ ሳይገባደድ የቀረ አይመስለኝም፡፡ እናንተ ግን የንስሃ ጊዜ አላችሁ፤ ተጠቀሙበት፡፡

ለጋራ ሀገር ዳግም ልደት የሁሉም ትብብርና ርብርብ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ ይሄ የድል አጥቢያ አርበኛ የሚሉት ትግልን ራቁት እሚያስቀር አባዜ ማስቀረት አለብን፡፡ በቅናትና በምቀኝነት የተጠላለፈ የነጻነት ትግል የትም አይደርስምና

ነገሮችን በቀናነት የመመልከት ባህልን እናዳብር፡፡ ካለመተማመን ይልቅ መተማመን የበለጠ ፍሬያማ መሆኑን እንገንዘብ፡፡ ሁሉም ሥራው ያውጣው፡፡ ከቃላት ይልቅ ተግባራችን እንዲናገር ዕድሉን እንስጠው፡፡ አንድ ሰው ከአንድ ሁኔታ ወደ ሌላ የተለዬ ሁኔታ ሊለወጥ የሚችልበትን አሳማኝ ምክንያት ከማጣራት ውጪ ተገቢ ነው ወይም አይደለም የሚባልበትን የጊዜ ርዝማኔ የደነገገ የለምና ዋናው ለውጣችን አማናዊ ይሁን እንጂ 5 ዓመት ከታገለው ግን ተጨባጭ ውጤት ማምጣት ካልቻለው ሰው ይልቅ በተለወጠ በቀናት ዕድሜ ውስጥ አመርቂ ውጤት የሚያስገኝ በአዲስ ጉልበት አስተዋፅዖውን የሚያበረክት ታጋይ ልዩ አድናቆትንና ሙገሣን ሊያገኝ ይገባል፤ በመሠረቱ እውነተኛ የነጻነት ተጋድሎ ከመሞጋገስና ከመኮሻሸት እንዲሁም ከአማሳኝ ውዳሴ ከንቱ መራቅ አለበት፤ ልብ ያመስግን፡፡ ስለሆነም ማንኛችንም ብንሆን በአስተዋፅዖዋችን እንዳኝ እንጂ በኋላ ታሪካችን ብቻ እንዳንወቀስ ወይም አላግባብ እንዳንሞገስ መጠንቀቅ ይገባል፡፡ ... ሃሳቤን ከዚህ አላስረዝም፡፡ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ፡፡ አሜን፡፡

ማሳሰቢያ ለሁሉም ድረ ገፆቻችን፡-

በሀገራችን ውስጥ በአሁኑ ወቅት ምንም መተንፈሻ የለንም፡፡ የወያኔው መንግሥት ሁሉንም የመረጃና የዜና በር ዘግቶ በራሱ ቲቪና ሬዲዮ ብቻ እንደሁልጊዜው ሁሉ የውሸትና የቤተ ሙከራ ቅንብር ቅስቀሳውን እየለቀቀብን ነው፡፡ ስለዚህ ለባለአድራሻዎቼ መልእክቴ እንዲደርስ በተቻላችሁ መጠን እተቀባበላችሁ ሁላችሁም ብታስተናግዱልኝ እጅግ ደስ ይለኛል፡፡ ማንንም ወገን ሆን ብዬ ለማስደሰት ወይ ለማስቀየም ያደረግሁት ነገር በፍጹም የለም፡፡ ባጋጣሚ ከምሬት የተነሳ የሚያስከፋ ቃል ወይ አንዳች ሃሳብ ቢገኝበት በመቻቻል በማለፍ ዋናው መልእክቴ ለሚመለከታቸው ወገኖች እንዲደርስልኝ ብታደርጉልኝ - ምን አደርግላችኋለሁ ልበል - አዎ፣ ብታደርሱልኝ በጸሎቴ አስባችኋለሁ፡፡ አሁንም እግዜር ይስጥልኝ፡፡ ፈጣሪ የመቻቻልንና የሆደ ሠፊነትን ባህል ያንግሥልን፡፡